# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

15



የታጠቀን ጠላት ለመቋቋም የጭቁን ሴቶች መታጠቅ አስፈላጊ ነው ።

ኅዳር ፴ — ፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# የተራማጆች ኅብረት

የየካቲት አብዮት ከፈነዳበት ወቅት አንሥቶ ከዚያም በፊት በኅቡዕ የተመሠረቱም ሆነ ከዚያ በኋላ የተቋቋሙ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ቡድኖች ሀልውናቸውን በልዩ ልዩ መንገድ እየገለጹ ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል ። በማንኛውም አብዮታዊ ትግል ወቅት በያለበት ብዙ ቡድኖች ብቅ ብቅ ማለታቸው የተለመደ ነገር ነው ።

እነዚህ የተለያዩ ቡድኖች እንደብዛታቸው የአቋም ልዩነት የላቸውም ። አፈጣጠራቸው በኅቡዕ ስለሆነና በመጀመሪያ ላይ በአንድ አካባቢ በትግል በተፈተኑና በሚተዋወቁ ጓዶች መሀል ስለሆነ አንድ ዓይነት አቋም ይዘው ልዩ ልዩ ቡድኖች ሊቋቋሙ ይችላሉ ። ትግሉ ቀስ በቀስ እየተፋፋመና ይፋ እየወጣ ሲሄድ ግን እነዚህ የተለያዩ ቡድኖች እየተዋወቁ ይሄዳሉ ። አንዳንዶቹ ልዩነቶቻቸውን በውይይት አስወግደው ይዋሀዳሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ አብዮቱ እየገፋ ሲሔድ ልዩነቶቻቸው እየሰፋ ፤ አሰላለፋቸው በተጻራሪ ሰፈሮች እየሆነ ጠላት ድርጅቶች ይሆናሉ።

የሆነ ሆኖ የአብዮቱ መግፋትና የመደቦች ትግል እየከረረ መሄድ ያሉትን ቡድኖች ሁሉ እንዲሸጋሸጉና ወይ በአብዮቱ ሰፈር ወይ በፀረ አብዮቱ ሰፈር እንዲቆሙ ያስገድዳቸዋል ። ከአብዮቱ መግፋትም ጋር የነዚህ ቡድኖች አሰላለፍ መድበስበሱ ይቀርና በአብዮት ወይ በፀረ አብዮት ሰፈር መቆማቸው ለማንም ግልጽ እየሆነ ይሄዳል ። እነዚህ ቡድኖች በሁለት ጠላት ሰፈሮች በመሸጋሸግ አያቆሙም ። አብዮቱ ሰፈር ያሉት ልዩነቶቻቸውን አጥፍተው ወይም አቻችለው ትግላቸውን በአብዮታዊ ግንባር ማስተባበር ይጥራሉ ። ፀረ አብዮት ሰፈር ያሉት ደግሞ እንደዚሁ ልዩነቶቻቸውን አጥፍተው ወይም አቻችለው ትግላቸውን በአንድ ፀረ አብዮት ግንባር ለማስተባበር ይጥራሉ ።

ከጥቂት ወራት ወዲህ በሀገራችን የፖለቲካ መድረክ ላይ በግልጽ መታየት የጀመረው ይኸው የሁለት ሰፈሮች የሁለት አቋሞች ፤ የሁለት ግንባሮች መልክ እየያዙ መምጣት ነው ። በአጠቃላይ ለመናገር የፀረ አብዮት ግንባር በተለይ በኢምፔሪያሊስቶች የረቀቀ አቀነባባሪነት ዛሬ ከፍተኛ የቅንብር ደረጃ ላይ ደርሷል ። የተራማጆች ግንባር ግን እስከዚህም አስተማማኝ የሆነ ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት ያስቸግራል ። በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች ማንኛውንም ችግርና ፈተና ተወጥተው ኃይላቸውን ማስተባበር ፤ ይኖርባቸዋል ። ተደጋግሞ እንደ ተነገረው የኢትዮጵያን አብዮት ከግቡ ሊያደርስ የሚችለው በጠንካራ የወዝአደር ፓርቲ የሚመራ ሰፊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዳር እስከዳር አቅፈው ማንቀሳቀስ የሚችሉ ተራማጅ ፓርቲዎችና ሕዝባዊና የሞያ ድርጅቶች የሚተባበሩበት አብዮታዊ ግንባር ሲኖር ብቻ ነው ።

በዚህ አብዮታዊ ግንባር ውስጥ ተሳትፎ የሚኖራቸውን ልዩ ልዩ ኃይሎች ጠንቅቆ ለማወቅና ለማስተባበር በአንዳንድ መሠረታዊ በሆኑ ጥያቄዎች እየተመሩ አብዮታዊ ቡድኖችን ከፀረ አብዮት ቡድኖች መለየት ያስፈልጋል ። በአብዮታዊው ግንባር የሚሰለፉትም ሆነ በፀረ አብዮት ግንባር የሚሰለፉት ኃይሎች በየሰፈራቸው ውስጥ ፍጹም የሆነ የአቋም አንድነት እንዲኖራቸው አያስፈልግም ። በሁለቱም ሰፈሮች ውስጣዊ ልዩነቶች ይኖራሉ ። ስለተራማጆች የትግል አንድነትና ስለ አብዮታዊ ግንባር በምናሰላስልበት ጊዜ በመጀመሪያ ማተኮር ያለብን በየሰፈሩ ባሉት ውስጣዊ ልዩነቶች ላይ መሆን የለበትም ። በቅድሚያ ማተኮር ያለብንና በግልጽ ማሳየት ያለብን በሁለቱ ሰፈሮች መካከል ያለውን የአቋም ልዩነት ነው ። ይህ በግልጽ ሳይታየን በተራማጆች ሰፈር ያለውን ልዩነት ልንተነትን ፤ ወይም ልንፈታ አንችልም ። ይህ በግልጽ ካልታየንና ዛሬ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ፀረ አብዮት ኃይሎች ያላቸው አቋም በግልጽ ካልተከሰተልን በተራማጆች ሰፈር ያለውን ልዩነት በማጋነን ፤ ከሚገባው በላይ ቦታ በመስጠት የአብዮታውያንን ሰፈር



እናዳክማለን ። ስለሆነም በተራማጆች ሰፈር ስላሉት የአቋም ልዩነቶች ከመተንተንና እነሱን ለመፍታት ከመታገል በፊት አድኃሪው ሰፈርና ተራማጅ ሰፈር በዋና ዋና የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ የሚወስዱትን አቋም መመርመርና ማወቅ ያስፈልጋል ።

በነዚህ ሁለት ጠላት ሰፈሮች መሀከል ያሉትን ልዩነቶች ብንመለከት በመጀመሪያ የማንኛውም አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ በሆነው በመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ ትልቅ ልዩነት እናያለን። በአብዮቱ ሰፈር የቆሙት ኃይሎች የኢትዮጵያ ጭቁኖች ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሰው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሚያቋቁሙት በተፋፋመው የመደቦች ትግል ገፍተው በነቃ ፤ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝብ ትግል ብቻ መሆኑን ያምናሉ ። ፀረ አብዮት ኃይሎች ግን ሕዝቡ ነቅቶ ተደራጅቶና ታጥቆ እውነተኛ ነፃነቱን እንዳይጐናጸፍ ፤ ከሕዝቡና ከአብዮቱ በፊት ራሳቸውን ከሥልጣን ላይ ለማውጣት ከምርጫ የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይጠይቃሉ።

ከዚሁ ጋር የተያያዘ የወዳጅና የጠላት ጥያቄ አለ ። በአብዮቱ ሰፈር የሚጠቃለሉት ኃይሎች የኢትዮጵያ ጭቁኖች ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝም ፤ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ናቸው ብለው ያምናሉ ። እነሱንም ይታገላሉ ። የፀረ አብዮቱ ሰፈር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠላቶች ሲዘረዝር ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን ከፊውዳሊዝም ፤ ከኢምፔሪያሊዝምና ከቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም የባሰ ጠላት አድርጐ ይቆጥራል ። ከነዚህ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ተዋሕዶ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን ለመጣል ይታገላል ።

በተጨማሪ የማንኛውም የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዋና ጥያቄ ተብሎ የሚገመተው የመሬት ጉዳይ አለ ። በዚህ ጥያቄ ላይ በአብዮቱ ሰፈር የተሰለፉ ኃይሎች የየካቲት ፳፭ ቀንን አዋጅ ይደግፋሉ ። በተለይ በመሬት በኩል የግል ሀብትን ፈጽሞ የሚያስወግደው የአዋጁ ይዘት ሙሉ በሙሉ የሚደገፍና የዚህ አዋጅ ዋና አብዮታዊ መልኩ መሆኑን ይቀበላሉ ። ፀረ አብዮቱ ሰፈር ያሉት ኃይሎች ኢ.ህ.አፓም ሆነ አባት ድርጅቱ ኢዲዩና ሌሎች አድኃሪ ቡድኖች በፕሮግራማቸው ላይ የየካቲት ፳፭ ቀንን አዋጅ አይደግፉም ። እንዲያውም ሁሉም ሌላ ዓይነትና በመሬት በኩል የግል ሀብትን እንደገና በመመለስ የየካቲት ፳፭ትን አዋጅ ዋና አብዮታዊ ይዘት የሚቀለብስ ፖሊሲ ይከተላሉ ።

በሁለቱ ሰፈሮች መሀከል ሌሎች ብዙ የልዩነቶች ነጥቦች አሉ ። ነገር ግን ሌሎቹ ልዩነቶች ከነዚህ መሠረታዊ አቋሞች የመነጩ እንጂ ራሳቸውን የቻሉ ልዩነቶች አይደሉም ። በአጠቃላይ ለመናገር ዛሬ በአብዮቱ ሰፈር የተሰለፉትና ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርን ለመመሥረት የሚበቁት ኃይሎች የየካቲት አብዮት እስከዛሬ ያስገኛቸውን ድሎች ለማንከባከብና ለመጠበቅ ይታገላሉ ። ለዚህም የነዚህ ድሎቻችንና የኢትዮጵያ ጭቁኖች ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝም ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ናቸው ብለው ያምናሉ ። እነዚህንም ለመደምሰስ የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል እንደሚያስፈልግ ተቀብለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲነቃ እንደደረጀና እንዲታጠቀ ይታገላሉ ።

ባጭሩ በነዚህ ነጥቦች ላይ የሚስማሙ ኃይሎች ተባብረው ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር መፍጠር ይችላሉ ። መፍጠርም አለባቸው ። ጥያቄው እንግዲህ ይህንን ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ዘላቂ ድል ዋስትና የሆነውን ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት ግንባር እንዴት እንመሥርተው የሚል ነው ።

ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደተገለጸው ይህ አብዮታዊ ግንባር በጠቅላላው በሀገሪቱ የሚገኙትን ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ከዳር እስከዳር ማንቀሳቀስ የሚችል ሕያውና ታጋይ ግንባር መሆን አለበት ። ለዚህም አብዮታዊ መደቦችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች ያስፈልጋሉ ። ነገር ግን ግንባር ማለት ፓርቲዎችን ብቻ ያቀፈ ድርጅት ማለት አይደለም ። በተጨማሪም ልዩ ልዩ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ የሙያ ማኅበራትንና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ያቅፋል ። ስለሆነም ከላይ የፈለግነውና ፀረ

አብዮቱን ግንባር ተቋቁሞ የኢትዮጵያን አብዮት ወደፊት ሊያራምድ የሚችለው ሕያው የሆነ ግንባር ሊመሠረት የሚችለው በነዚህ በሚሊዮን የሚቆጠረውን ሰፊ ሕዝብና ወገኖቹን በልዩ ልዩ ደረጃዎች አደራጅተውና እንቅስቃሴው ለአብዮቱ ሊያሰልፉ በሚችሉ ፓርቲዎችና ሌሎች ድርጅቶች አባልነት ነው ።

ስለሆነም አብዮታዊ ግንባር ለማቋቋም በአሁኑ ጊዜ ለዚህ ግንባር ሕያውነት ፤ ታጋይነት ፤ ሕዝባዊነትና አብዮታዊነት ዋስትና የሚሆነው የሰፊው ሕዝብ በየደረጃው መደራጀት ስለሆነ በዚህ በኩል የተፋፋመ ትግል ማካሔድ ያስፈልጋል ። አሁን በምንገኝበት የዚህ አብዮታዊ ግንባር ጥያቄ አንገብጋቢ በሆነበት ወቅት ወደሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር የሚወስደን የዲሞክራሲ መሰላል ጥያቄ ይበልጡን አንገብጋቢ ሆኖ የምናገኘው እዚህ ላይ ነው ። በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እንደ አጣዳፊ ተግባር ተቀጥሮ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ለመማር ፤ ለማስተማር ለመደራጀትና ለማደራጀት አስፈላጊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ ክሥራ ላይ ይውላሉ የተባለውም ለዚህ ነው ።

ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ከፍ ብለን በጠቀስናቸው መለኪያዎች አማካይነት ከአብዮታዊው ሰፈር የሚጠቃለሉት ኃይሎች በይበልጥ እንዲደራጁ ፤ በሕዝቡ ውስጥ በይበልጥ እንዲገቡ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ ያስፈልጓቸዋል ። ግን ዲሞክራሲያዊ መብቶች አስፈላጊ የሚሆኑት ሰፊውን ሕዝብ ለማደራጀት ብቻ አይደለም ። በተራማጅ ግንባር ቀደም ኃይሎች መሀከል ያሉትና የማይካዱት መለስተኛ ልዩነቶች በግልጽ እንዲታወቁና ከሚገባቸው በላይ ሳይጋነኑ እንዲፈቱ የግድ በነዚህ ግንባር ቀደም ኃይሎች መሀከል በሰፊው ሕዝብ ፊት የሚካሄድ ውይይት ያስፈልጋል ። እንዲህ ዓይነቱ ውይይት ካታፈነ የአብዮታውያን አንድነት በጠነከረ መሠረት ላይ ሊገነባ አይችልም ። ያሉት ልዩነቶች ወይ ተድበስብሰው ይታፈኑና የእንቧይ ካብ አንድነት ይሆናል ፤ ወይ ከመጠን በላይ ይጋነኑና ለአድኃሪዎችና ለቀልባሽ ኃይሎች በአብዮቱ ግንባር ሠርገው የሚገቡበት ቀዳዳ ይፈጠራል ። በሁሉም በኩል ቢሆን የዲሞክራሲያዊ ውይይት መታፈን ፤ የዲሞክራሲያዊ መብቶች መዘግየት የሚያግዘው የፀረ አብዮቱን ግንባር ነው ።

የሆነ ሆኖ ይህ ስለተባለ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር እስኪፈጠር ድረስ ተራማጅ ኃይሎች መተባበርና በአንድነት መቆም አይችሉም ማለት አይደለም ። በአንድነት መቆም ይችላሉ ። በአንድነት መቆም አለባቸው ። እንዲያውም ጠንካራ የሆነ ኅብረት የሚገነባው በጠረጴዛ አካባቢ በሚደረግ ውይይት ብቻ ሳይሆን ከፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር በሚደረገው የዕለት ከዕለት ትግል ሳቢያ በትግሉ ሜዳ ላይ በሚታየው የተግባር አንድነት መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለሆነም ዛሬ በፀረ አብዮቱ ሰፈር ያሉት ኃይሎች ኃይላቸውን ያስተባብራሉና አብዮታውያንም እንደዚሁ የዚህን ግንባር መፈጠር ሳይጠብቁ ፤ ወደዚያውም እየሠሩ በተግባር ትብብራቸውን ማጠንከር ፤ በትግል ፈተና ውስጥ ይበልጥ መተዋወቅ ፤ ይበልጥ የመተማመንና የጓድነት መንፈስ እንዲሰፍን መታገል አለባቸው ።

ዞሮ ዞሮ ልዩነቱ በሁለት ጠላት ሰፈሮች መሀከል ነው ። አንዱ አብዮቱ እንዲገፋ ሌላው ደግሞ እንዲቀለበስ ይታገላል ። ተራማጆች በሙሉ ይህንን ሀቅ ተገንዝበው በመሀከላቸው ያለው ልዩነት በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ልዩነት እንደሆነና ዛሬ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ከቀልባሽ ኃይሎች ጋር ከሚያደርጉት የሞት ሽረት ትግል አንፃር ሲታይ ኢምንት እንደሆነ መገንዘብ ይኖርባቸዋል ። አንዳንድ ተራማጆች ዛሬ ይህ ባይገባቸው ፤ በተራማጆች መሀል ያሉትን ቅራኔዎች ትክክለኛ ቦታቸውን ማስያዝ ቢያቅታቸው ይህ አደገኛ ሁኔታ የመጣው ከዲሞክራሲና ከሰፊ ውይይት ጉድለት እንደሆነ ግልጽ ነው ። ስለሆነም ሰፊውን ሕዝብ ለማስተማርና ለማደራጀት ብቻ ሳይሆን በተራማጅ ግንባር ቀደም ኃይሎች መሀከልም የጠነከረ አንድነት ለመፍጠር ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ዲሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች የሚለው መፈክር አንገብጋቢ ሆኖ ይታየናል ።

ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ
አብዮታዊት ኢትዮጵያ ።